# በግብርና ሚኒስቴር
# እና
# አስካይ እርሻ ልማት ኃ/የተ/የግል ማህበር መካከል የተፈፀመ
# የመሬት ኪራይ ውል ስምምነት

ይህ የመሬት ኪራይ ውል ስምምነት በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር አድራሻው በቦሌ ክ/ከተማ አዲስ አበባ ; ኢትዮጵያ የሚገኝ መሆኑ እና ከዚህ በኋላ ‹‹አከራይ›› በመባል በሚታወቀው

እና

*አስካይ እርሻ ልማት ኃ/የተ/የግል ማህበር* በማህበራት ህግ መሠረት በኢትዮጵያ የተቋቋመና ከዚህ በማስከተል ‹‹ተከራይ›› በመባል የሚጠቀሰው አድራሻ *ትግራይ* ክልል *አክሱም ከተማ* ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር *አዲስ* ስ.ቁ *0913-522471* መካከል ተፈፅሟል፡፡ ተከራይ የሚለው አባባል እንደ አገባቡ የማህበሩን ተተኪዎች/ወራሾች እንዲሁም ወኪሎች የሚመለከት ነው፡፡

ተከራይ በጥጥ ልማት ለመሰማራት በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የተቋቋመና *በቤንሻንጉል ጉሙዝ* ክልል ውስጥ ለልማቱ በቂ የሆነ መሬት በመፈለጉ፣

አከራይ አስፈላጊውን መሬት ቀጥሎ በተዘረዘሩት የውል ቃሎችና ሁኔታዎች መሰረት ለተከራይ ለመስጠት ፈቃደኛ በመሆኑ፤

ተዋዋይ ወገኖች በ *10/07/2003* ዓ.ም ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች መሰረት ይህንን የመሬት ሊዝ ስምምነት ፈጽመዋል፡፡

## አንቀጽ 1

## የስምምነቱ ወሰን

1.1 የዚህ የሊዝ ስምምነት ወሰን በረዥም ጊዜ የመሬት ሊዝ *በቤንሻንጉል ጉሙዝ* ክልል *መተከል* ዞን *ዳንጉር* ወረዳ *አባይዳር* ቀበሌ ውስጥ በ *3,000* ሄ/ር መሬት ላይ *የጥጥ* እርሻ ለማቋቋም ነው፡፡ መሬቱም በዚሁ አግባብ የሚከራየው መሬቱን በአግባቡ የመጠቀም እንዲሁም በመሬቱ ላይ የሚገኙ፣ መዋቅሮች፣ ተከላዎች፣ ንብረቶች እና ሌሎች በመሬቱ ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎችን ለስራው ዓላማ ተግባራዊ ማድረግን የሚያካትት በመሆኑ፣

1.2 ይህ የመሬት ኪራይ ስምምነት ከዚህ በማስከተል "የኪራይ መሬት" በመባል የሚጠቀሰውን የገጠር መሬት ሙሉ በሙሉ እና በብቸኝነት ለመጠቀምና በዚህ ስምምነት በአንቀጽ ሁለት በግልጽ የተቀመጠውን የኪራይ ክፍያ ብቻ ለመክፈል የተፈፀመ ነው፡፡

ግብርና ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Agriculture